# ኣሳሳቢው የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ሁኔታ በኢትዮጵያ

እንደሚታወቀው ሁሉ የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ማቋቋም በተለያዩ ኣገሮች ሰፋፊ የልማት ታፔላዎች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እነዚህ ተቋማት በርካታ የሰው ሃይል ወደ ስራ እንዲሰማራና ጥቂት የማይባል ካፒታል እንዲጠራቀም የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሰፊ የስራ እድልና መጠነኛ ካፒታል የማጠራቀም ሂደት እንዲረጋገጥ በማድረግ መተኪያ የሌለው ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ኣገሮች በስፋት የሚሄዱበት ስራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህ ግን በተለያዩ ኣካባቢዎችና ኣገሮች በተመሳሳይ ሂደት፣ ደረጃና ውጤታማነት የሚታይ ኣይደለም፡፡ በበለፀጉት ኣገሮችና በመበልፀግ ላይ የሚገኙ እንደ የሩቅ ምስራቅ ኣገሮች ሰፊና ቀጣይነት ያለው እድገት የሚታይባቸው ጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እናያለን፡፡ እንደ ኣፍሪካ የመሳሰሉ ያልበለፀጉ ኣገሮች የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ጭልምልም ሲሉና እድገታቸው ተገድቦ የቀረበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በተለያዩ ኣገሮች የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እድገት ለምን ሊለያይ ቻለ? በኣንዳንዶቹ ኣካባቢዎች ደግሞ ለምን እንደተጠበቀው ለውጥ የማሳዩበት ሁኔታ ተፈጠረ? የሚለው ጉዳይ ማየት በጣም ኣስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የተለያዩ ምክንያቶች ኣሉት፡፡ ኣንደኛ እነኚህ የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት የተቋቋሙበት ቴክኒካዊ መሰረት የተለያየ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ ቀጣይነት ያለው የጥሬ እቃ ኣቅርቦት ያለመኖር ፣ ያመረትዋቸው ሸቀጦች ገበያ ማጣት፣ ለዚህ የሚያስችል የብድርና ገንዘብ በባንክ የማስቀመጥ ስርኣት ያለመኖርና በሌሎች ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ የሚነሳ በሩቅ ምስራቅ የሚገኙት ኣገሮች ያሉት የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት በኣካባቢያቸው ከሚገኑ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ተሳስረው እንዲቋቋሙና እንዲያድጉ ስለሚደረግ የተሻለ እድገትና ከፍተኛ ውጤት ይታይባቸዋል፡፡ እንዲሁም የጠበቀ ትስስር ከኣካባቢ ስልጠና፣ ቴክኒክና ሞያ መኣከላት እንዲኖራቸውና ኣቅማቸው በዚህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያደርግ ሁኔታ ስላለ ቴክኒካዊ ኣቅማቸው ተወዳዳሪና የማምረትና የፈጠራ ችሎታቸው ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም በቅርብ በተሻለ ዋጋ ጥሬ እቃ የሚያገኙበትና በዚህ ላይ የተመሰረተ ኣቅማቸው በቀጣይነት እንዲያሳድጉ ስለሚረዳቸው ስፋታቸውና ጥንካሬኣቸው ይበልጥ ከፍ እያለ ይሄዳል፡፡ ምርታቸውን የሚጠቀም ሰፊ የኣገር ውስጥ ገበያ ስለሚኖር የገበያ መጥበብና የዋጋ መናር ችግር ኣያጋጥማቸውም፡፡ ቀጣይነት ያለው እድገት፣ገንዘብ የማካበት፣ የፈጠራ ስራና ኣዲስ ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚታይባቸው ይሆናሉ፡፡ ከዚህ የሚነሳ የምርታማነት ደረጃቸውና ስፋታቸው እያደገ የመሄድ ሁኔታ ይኖራል፡፡ በኣፍሪካና ሌሎች ያልበለፀጉ ኣገሮች ግን

ከኢንዱስትሪ ጋር ይህን የሚባል ቁርኝት የላቸውም፡፡ በየጊዜው የግብኣቶች ኣቅርቦትና ገበያ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ ለተገኘው ጥቂት የውጭ ምንዛሪ እየተሻሙ እንዲኖሩና ከርካሽ የውጭ ሸቀጦች ጋር እየተወዳደሩ ሊወጡት ወደማይችሉት የድህነት ኣዙሪት ሲገቡ ይታያሉ፡፡ ኣንደኛ በቀጣይነት ኣቅምን የሚያሳድግና ቴክኒካዊ መሰረታቸው የሚያሰፋ የስልጠና ስርዓት ስላልተፈጠረላቸው ነው፡፡ እዚህ የሚኖራቸው የእዳ ቁልልና ከፍተኛ ወለድ ፣ የማሕበራት ተነሳሽነትና ፈጠራን የማፍለቅ ችሎታ የሚገድል ኣደረጃጀትና የገዥ ፓርቲ ጣልቃ ገብነት የፈጠረው ችግር ሰንጥቀው ማለፍ ያቅታቸዋል፡፡ ይህ  የገዥ ፓርቲ ታፔላዎች ከመሆን ያለፈ ሌላ የካፒታል ኣቅም የሚፈጥር ኣይደለም፡፡ ስለሆነም እንደ ኣሸን እንዲቋቋሙ የተደረገ ቢሆኑም በድምር ሂደታቸው እየከሰሙ መሆናቸውን እየታዘብን ነው፡፡

በሌሎች የኣፍሪካ ኣገሮች እንዳየነው ሁሉ በኣገራችንም በይፋ የተቋቋሙ እንዱስትሪዎችና የኣገልግሎት መኣከላት የሉም፡፡ ኣሉ የሚባሉት የቴክስታይልና ብረታ ብረት ፋብሪካዎችም እርስበርሳቸው የተቆራኙና የሚመጋገቡ ሳይሆን ለስም ያህል እንደ ተቋምና ፋብሪካ ራሳቸውን ችለው የቆሙበት ሁኔታ ኣይታይም፡፡ እርስበርሳቸው እየተመጋገቡ የኣንዱን ጥሬ እቃ ኣቅርቦት የሚያሟላበት ሁኔታ በሚያመቻች መንገድ ኣልተቋቋሙም፡፡ እንደ ቀለም፣ ቁልፍና ሌሎች ኣንድ እቃ ሙሉ ሆኖ የሚመረትበት ግብኣቶች  ከውጭ ኣገር የሚመጡበት ኣሰራር ነው የሚታየው፡፡ ይህ ላለን የውጥ ምንዛሪ እጥረት እየባሰ እንዲሄድ የሚያደርግና ምርቶቻችንም ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ በእንዱስትሪዎቻችን   ላይ የታሰረ ወጥመድ ነው፡፡ ኣሉ የሚባሉ ጥቂት ኢንዱስትሪዎችም ለጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ጥላ ሊሆንዋቸው በሚያስችል መልኩ የተቋቋሙ ኣይደሉም፡፡ በመካከለኛና ትላልቅ እንዱስትሪዎች ደረጃ የሚታዩ እድገታቸው ደካማ ነው ብቻ ሳይሆን በተለይ እንደኛ ባሉ ክልሎች ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ እዚህ ብዙ ያልተሰራበትና የእንፉቅቅ ጉዞ በመጓዝ ላይ መሆናቸውን ነው የሚታየው፡፡ በኣገራችን ያለው የካፒታል እጥረት በስፋት ይነገርለት ይሆናል እንጂ መንግስትና ባለሃብቶች በጋራ በመስራት፣ ያለው ውሱን ሃብት ብዙ ምርት በማይገኝበትና ውጤታማ በሆነ መንገድ በስራ ላይ ሳይውል የሚባክን ሃብት ትንሽ ኣይደለም፡፡ ስለዚህ ህወሓት/ኢህኣዴግ ድክመቶቹን በመሸፋፈን ጥቀቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት  ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲጠቀምባቸው ይታያል፡፡

ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ጥቀቃቅንና ኣነስተኛ ተቋሚት  ከከተማ ልማት ፓኬጅ ጋር በማስተሳሰር እንዲያብቡ የተሞከረበት ሁኔታ ኣለ፡፡ ነገር ግን እነኚህን የሚከታተል ኣካል በየግዜው ኣደረጃጀቱ ይቀያየራል፡፡ የተዘረጋው የደደቢት የብድር ስርኣትም በከፍተኛ ወለድ ለበርካታ ማህበራት ብዙ

ብድር የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ብዙ ህዝብና ማህበራት ከፍተኛ ብድር የወሰዱበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ለዚህ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚወሰዱ አሰራሮችና አደረጃጀቶችም አሉ፡፡ አንደኛ በማህበር/ በሽርክና ለመደራጀት የንግድና ኢንዱስትሪ ፅ/ቤት ከገዢው ፓርቲ የጠበቀ ዝምድና በሚፈጥር መልኩ በማደራጀት የገዥው ፓርቲ መሳርያ እንዲሆኑ ይገደዳሉ፡፡ በተወሰነላቸው የስራ ዘርፍ ውስጥ ገብተው እንዲሰሩም ጫና ይደረግላቸዋል፡፡ አሉ የሚባሉት ኢንዱስትሪዎች፣ ፋብሪካዎችና የግል ጋሎት መአከላትም ለጥቀቃቅንና አነስተኛ ተቛማት ግብኣቶች አቅራቢና ምርታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገው አልተደራጁም፡፡ ተመጋጋቢዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህ ምንም የእርስበርስ ቁርኝት የላቸውም፡፡ እያንዳንዱ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቛም የሚያስፈልጋት ጥሬ እቃም ሆነ ሌላ ከውጭ አገር ነው የሚመጣው፡፡ ያመረተችው ምርትም ከውጭ አገር ከሚመጡ ሸቀጦች በጠባብ ገበያ እየተወዳደረች እንድትሸጥ ትሞክራለች፡፡ በዚህ ምክንያት የተጠራቀመው እዳ እንዴት መመለስ ትችላለች? በዚህ መንገድ በየግዜው እንደ እንቁላል የሚፈለፈሉ ማህበራት እንደተጠበቁት በካፒታል አቅማቸው ሳይመረቁ ሲፈርሱና ሌላ አማራጭ ሲፈልጉና አዲስ ማህበራት ሲቛቛሙ እናያለን፡፡ እንደ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ዘገባ ከሆነ ሁሉም የሞቱትም ያሉትም የወደቁትም ያልወደቁትም እንደ ድል ተደርጎ ስለሚዘገብ አሃዛዊ መረጃ በሽ ነው፡፡ እዚህ ከሺዎች አልፎ አልፎ እዳቸው የመለሱና የተወሰነ ካፒታል ያጠራቀሙ የሉም ማለት አይደለም፡፡ በአገራችን /ክልላችን በመቛቛም ላይ ያሉ አነስተኛና ጥቃቅን ተቛማት አሁን በያዙት መንገድ ሊሄዱ ስለማይችሉ በሚከተሉት አቅጣጫና አካሄድ መሰረታዊ ማስተካከያ ካልተደረገላቸው በአፍሪካ ካሉት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቛማት የተለየ እድል ሊያጋጥማቸው ይችላል የሚል እምነት የለንም፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ ተቛማት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ሰፊና መሰረታወዊ መሆኑ ከላይ በዝርዝር አይተነዋል፡፡ አንደኛ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቛማት አካል ወይም እንደ አደረጃጀት ከአንድ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ወደ ሌላው ሲሸጋገር በመጨረሻ ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ተቛማት ያድጋል በዚህ አድርጎ በአገር/ክልል ኢንዱስትሪ እንገነባለን የሚል የህወሓት/ኢህአዴግ አስተሳሰብ ሳያረጅ ሸበት ያወጣ አስተሳሰብ ነው እንላለን፡፡ ኢህአዴግ ባስቀመጥኩት መንገድ ማህበራት በየግዜው ካፒታል አጠራቅመው ሲሰጣቸው ከነበረ ድጋፍና የቅርብ ክትትል ወጥተው በስራ በልጠው ወደ ነፃ ውድድር ሊገቡ ይችላሉ ይላል፡፡ እስከ አሁን ስንቶቹ ተመርቀው ወደ ነፃ ገበያ ስርአት ገብተዋል ካልን መልስ አናገኝበትም፡፡ እነዚህ በምንም የእውቀትና ችሎታ ተደማሪነት የሌለው የገዥ ፓርቲ አባል ለመሆን ፈቃደኛ ስለሆኑ ብቻ ስሚንቶ በማከፋፈል የተሰማሩትም ሲበተኑ እንጂ ሲመረቁ አልታዩም፡፡ በመቀሌ በደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቛም ከስልሳ ስድስት ሚሊዮን/66,000,000/

ብር በላይ የሚገመት ብድር ለበርካታ ማህበራት ተሰጥተዋል ፡፡ በዚህ መንገድ ካፒታል ኣጠራቅመው የተመረቁ በጣት የሚቆጠሩ ማህበራት ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ምን ያህሉ ናቸው ብድራቸው የመለሱ፣ የተጠራቀመ እዳ የሌላቸውና ከእዳ ነፃ የሆኑ ብለን ከጠየቅን ከ70% ማህበራት በላይ እዳቸውን ያልመለሱ፣ የጠፉና የተበታተኑ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ያለው ችግር ኣንደኛ በኣግባቡ ተደራጅተው ኣመርቂ ውጤት ያለማምጣታቸው ብቻ ሳይሆን እዳቸውን ሳይመልሱ የተበተኑ ማህበራት ብዙ መሆናቸው ነው፡፡ እፎይታና መረጋጋት በሌለበት ሁኔታ ከሰለጠኑበት ሞያ በታች እየሰራ የሚገኘው የሰው ሃይል ብዙ መሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልገው እውነት ነው፡፡ እንደ ልምድ በማህበራት በተደጋጋሚ የሚታይ መደራጀት፣መበተን፣ መረጋጋት የሌለው ስራ መስራት ከዚህ የተነሳ በማህበራት ተስፋ መቁረጥና እፎይታ ማጣት ሰፊ ነው፡፡

ዓረና ትግራይ ጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እንዲፈጠሩ፣ እንዲያብቡ፣ እያደጉና እየተጠናከሩ እንዲሄዱ በኣገራችን ልማትና ድህነት ደረጃ በደረጃ በመቀነስ መተኪያ የሌለው ሚናቸውን መጫወት እንዳለባቸው ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ የሚደራጁበትና የሚመሩበት ያለው ኣቅጣጫ ጤናማ ኣይደለም ባይ ነው፡፡ በማህበራቸው ኣባላት ነፃ ፍላጎት ሲመሰረቱ ደግሞ ቀስ በቀስ ወደ ህወሓት/ኢህኣዴግ ፖለቲካ መሳርያነት ካልተሸጋገሩ ብድር፣ ስልጠናና ሌላ ኣስተዳደራዊ ድጋፍ በማጣት እንዲከስሙ ይደረጋል፡፡ በነፃነት ያልተፈጠረና በነፃነት የማይንቀሳቀስ ኢኮኖሚያዊ ተቋም ደግሞ ዘለቂነት ሊኖረው ኣይችልም፡፡ የተቆጣጠረው ሃይል ኣያስፈልገኝም ባለበት ጊዜ የሚሞት ነው፡፡ ካልሆነም እድገቱ የተገደበ ይሆናል፡፡

ሌላው ደግሞ በጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ብቻ የኣገር እድገት ኣይመጣም፡፡ ከዚህ ጎንለጎን ጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እንዲያብቡ መሰረት የሚጥሉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የነሱን ምርቶች በግብኣትነት የሚጠቀሙ መካከለኛና ትላልቅ ተቋማት መኖር ኣለባቸው፡፡ የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እድገት ቀጣይና ኣስተማማኝ እንዲሆን እንደዚህ ኣይነት ትስስርና መደጋገፍ መኖር ኣለበት የሚል እምነት ኣለን፡፡ ልክ ነው ኣንዳንድ ኣነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሚኖራቸው ነፃ እንቅስቃሴ ወደ መካከለኛና ትላልቅ ተቋማት መሸጋገር ይችላሉ፡፡ ሁሉም ግን የዚህ እድል ተቋዳሽ ኣይሆኑም፡፡ ኢኮኖሚ እድገትና ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ጋር ጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት እያበቡና እየሰፉ ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ መንግስት ይህ የጠበቀ ትስስር እንዲፈጠር ተገቢ ጥረት ማድረግ ኣለበት፡፡ ለነፃ ኢቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት ኣለበት፡፡ ለመካከለኛና ትላልቅ ተቋማት እድገት ኣስፈላጊ ማበረታቻዎች መቅረፅ ኣለበት፡፡ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ለፖለቲካዊ ኣላማ መሳርያነትና ከገዥ ፓርቲ ጥገኝነት ነፃ መውጣት ኣለባቸው፡፡

ስለዚህ የጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት የልማት ታፔላዎች እንደመሆናቸው መጠን በግለሰብ ፣ ቡድን፣ ኣካባቢና ኣገር ሰፊ የልማት ለውጥ በማምጣት የራሳቸው ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ በጠቅላላ በኣገሪቱ የሚመዘገበው ለውጥ የልማት ታፔላዎች የሚፈጥሩት ሰፊ የስራ እድል ፣ ካፒታል በማጠራቀም፣ የሚኖራቸው ፋይዳና እንዲሁም ቴክኖሎጂ ሽግግር ይነስም ይብዛም ከሚጫወቱት ሚና የሚነሳ ነው፡፡ ይህ በሰፊው ኣቅም እየፈጠረ እንዳይሄድና በተሟላ መንገድ ዳገት እንዳይወጣ የተቀመጠለት ጠንካራ ቴክኒካዊ መሰረት ያለመኖር ጉዞው ይገድበዋል፡፡ ይህ ኣንድ ማነቆ ሆኖ ሌላ ተጨማሪ የባሰ ማነቆ የሚኖረው ደግሞ ጉዞው በፖለቲካ የተጠፈረ መሆኑ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ጭንቀት የፈጠረው ስልት ከመሆን ኣልፎ ኣስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ ሌላው ተጨባጭ በጥቃቅንና ኣነስተኛ ተቋማት ያለው ስራ ስናይ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ ኣደረጃጀትና የይድረስ ይድረስ የዘመቻ ስራ በመሆኑ ኣመርቂ ውጤት ኣይታይም፡፡ ችግሮች የሚያስተዳድር ኣመራር እንጂ ከችግር የሚያስወጣ ኣመራር የላቸውም፡፡ ለማህበራት የሚሰጠው ድጋፍና የተዘረጋው የስልጠና ስርኣት ስናይ የኣገርን ሃብት ከማባከን ኣልፎ ተጨባጭ ለውጥ ኣያመጣም፡፡ ፋይዳው ከፕሮፖጋንዳ ፍጆታነት ኣያልፍም፡፡ በዚህ የሚሰማራው የኣገር ሃብት በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ጥርት ያለ ኣሰራር የተከተለ ስላልሆነ መኣከሉ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግበስበስ በመሆኑ የኣገር ሃብት እየባከነ ነው፡፡

የዓረና መንገድ ለነዚህ ችግሮች በመሰረቱ በማስወገድ በየደረጃው እያደጉና እየተጠናከሩ እንዲሄዱ የሚያደርግ ቴክኒካዊ መሰረትና የስልጠና ስርኣት በመፍጠር በማህበራት ነፃነትና ተጨባጭ የህዝባችን ኣቅም ያገናዘበ የብድር ስርኣት፣ የኣካባቢ ሃብት ተዛማጅነትና የህዝባችን ማተርያላዊ ኣቅም መሰረት በማድረግ ኣስተማማኝና ለውጥ ኣምጪ ኣነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት እንፈጥራለን ፡፡ እነዚህ በየግዜው የሚደራጁና የሚስፋፉ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በኣገራችን ኢኮኖሚ እርስበርሱ እያስተሳሰሩና እንዲመጋገቡ እያደረጉ በኣገራችን ኢኮኖሚ ጠንካራና ራሱን የቻለ ተነፃፃሪ ነፃነቱ የጠበቀ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡

ኣሮን